# የACPS Express 4/14/2023: የሱፐስ ስፖትላይት (Supe's Spotlight— የኤፐሪል (April) የቪዲዮ መልዕክት

## የ'ሱፐ ስፖትላይት (Supe's Spotlight)': የኤፐሪል (April) የቪዲዮ መልዕክት




በኤፐሪል (April) ወር ውስጥ፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ለትምህርት ቤቶቻችን እና ተማሪዎቻንች ጥቅም-ላስገኙ - በርካታ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - ያበረከቱትን ግሩም-የሆነ ስራቸውን አክብሯል። የዚህ ወር [የ'ሱፐ ስፖትላይት (Supe's Spotlight)' - ጠቅላይ ስራ-አስኪያጅ ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) የአሌክሳንድርያ በጎ-ፈቃደኛን በጎበኙበት ጊዜ፣ ትኩረቱን በጎ-ፈቃደኛነት ላይ ያደረገ]() እና በትምህርት ቤት አካባቢያችን ውስጥ፣ በልገሳ-መስጠት ምን-ዓይነት ለውጥን እንደሚያመጣ ያንጸባረቀ-ነው። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞቻችን፣ ለትምህርት ቤት ክፍል/division ለሚያደርጉትን-ሁሉ፤ ACPS በእጅጉ-አድናቆትን ይገልፃል። እናመሰግናለን!

## እናመሰግናለን፤ የACPS ረዳት ርዕሰ-መምህራን!




ከኤፐሪል (April) 10 ቀን እስከ ኤፐሪል (April) 14 ቀን 2023 ድረስ፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ብሄራዊ የረዳት ርዕሰ-መምህራኖች ሣምንትን - አክብሯል። ረዳት ርዕሰ-መምህራኖች፣ ለማስተማር እና መማር አዎንታዊ የሆኑ እሴቶች መኖራቸውን በማረጋገጥ ላይ ወሳኝ-የሆነ ሚናን ይጫወታሉ፣ እና ለተማሪዎቻችን እና ትምህርት ቤቶች የሚያሳዩትን ቁርጠኝነት እውቅና-እንሰጠዋለን። ለተከሰቱ-ክስተቶች ቁጥር-ስፍር በሌለው ጊዜ የተገኙ፣ ተማሪዎችን በየቀኑ የሚረዱ፣ እና በመንገዳቸው ላይ የሚመጡ ፈታኝና-አስቸጋሪ ነገሮች ላይ ምላሽ-ይሰጣሉ።

"የACPS ረዳት ርዕሰ-መምህራኖች - ተማሪዎችን ለመርዳት ከሚገባው በላይ የሚሄዱ፣ ተማሪዎች የሚያበረታቱ እና የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህሮቻቸውን የሚረዱ-ናቸው፣" ብለዋል የACPS ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)።

“ረዳት ርዕሰ-መምህራኖቻችን - ለሚያሳዩት ትጋት እና የፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም (Equity For All) - ዋናው ዕቅድ (Strategic Plan) - በትምህርት ቤታችን ክፍል/division ውስጥ ወደፊት ገፍቶ እንዲጓዝ ለሚያደርጉት ሁሉ፤ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።”

የACPS 18 ትምህርት ቤቶች - ረዳት ርዕሰ-መምህራኖቻቸውን በሣምንቱ-ሙሉ፣ ፎተግራፎችን በማጋራት እና የምስጋና ቃላቶችን #ACPSAPsን በመጠቀም፤ አክብረዋቸዋል። የለጠፍናቸውን/posts በፌስቡክ/Facebook፣ ትዊተር/Twitter እና ኢንስተግራም/Instagram ላይ ተመልከቱ።

ረዳት ርዕሰ-መምህራኖቻችን - አመራርነት፣ ቁርጠኝነት እና ውሳኔን መወሰን ላይ-በሚያስፈልግ ጊዜ፤ ከሁሉ-ልቀው ተገኝተዋል። በተማሪዎቻችን ስኬት ላይ ረዳት ርዕሰ-መምህራኖቻችን ያላቸውን አስተዋጽዖ፣ ከፍተኛ-ክብር እንሰጠዋለን። በእውነቱ - በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ፣ ብዙ-ያልተዘመረላቸው ጀግኖች-ናቸው።

## የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ - ወሳኝ-በሆነው የዳሰሳ-ጥናት አማካኝነት፣ ባለድርሻ-አባላቶች (Stakeholders) ያላቸውን ሃሳብ እንዲያጋሩ ጠየቀ



የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ - ማህበረሰባችንን የሚያገለግለው የትምህርት ቤት ቦርድን መዋቅር የሚነካውን ቁልፍ-ስለሆኑ ጉዳዮች በተዘጋጀው የዳሰሳ-ጥናት ላይ፣ ሁሉም የባለድርሻ-አባላቶች (stakeholders) እንዲካፈሉ እየጠየቀ-ነው። ይህ የዳሰሳ-ጥናት፤ በበርካታ-ቋንቋዎች በኦንላይን-ላይ፣ እስከ 11:59 p.m. ድረስ - በኤፕሪል (April) 26 ቀን 2023 ድረስ፤ ክፍት-ሆኖ የሚገኝ-ይሆናል።

በቅርብ ወራቶች ውስጥ፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን በተሻለ-ሁኔታ ለማገልገል፣ የትምህርት ቤት ቦርድ መዋቅርን እንደግና-ለመቅረጽ፤ ቦርዱ በዚህ-ጉዞ ውስጥ ተሰማርቶ-ይገኛል። የቦርድ አባል ምርጫዎችን ለመለወጥ ከግምት-ውስጥ ያስገባ ሲሆን፤ ተለዋዋጭነት-ያለው ተርሞች/staggered terms፣ የተርሞችን ርዝመት እና የቦርድ አባላቶችን ቁጥርን አካትቶ የሚጨምር-ይሆናል።

ማህበረሰቡ ከለመደው ነገር አንዱ የተለየ ነገር እና ዋናው ክፍል-ሆኖ ከግምት-ውስጥ የገባው፤ “ተለዋዋጭነት-ያለው ተርሞች/staggered terms” ነው። ይህ ሲተነተን፤ የትምህርት ቤት ቦርድ አባላቶች በተለያየ ዓመታት መመረጣቸው፣ የትምህርት ቤት ቦርድ አገልግሎት የመጀመሪያ እና የማብቂያው ተርሞች/terms ጊዜያቸው-በተለያየ ጊዜ መሆን ላይ - ሁሉንም በአንድ-ጊዜ ከማድረግ-ይልቅ፤ አድርጎ-የሚያስናዳ-ነው። በአሁኑ-ጊዜ፤ ሁሉም - ዘጠኝ የትምህርት ቤት ቦርድ አባላቶች፤ በዚያው-በአንድ ምርጫ በዚያ-አንድ በሆነ ዓመት ውስጥ ይመረጣሉ - የአገልግሎት ተርማቸውም በአንድ-ዓይነት ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል። ‘ተለዋዋጭነት-ያለው ተርሞች/staggered terms’፣ ለአማላቶች በተለያየ ዓመታት እንዲመረጡ የሚያደግ፣ ሲያገለግሉ የነበሩ አንዳንድ አባላቶችን ቦርዱ እንዲያቆይ ማድረግን-ለማረጋገጥ፤ አገልግሎት-አሰጣጡ እና የተቋማዊ እውቀቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል። በተጨማሪም፤ አዲስ የቦርድ አባላቶችን ወደ ክፍሉ/division ስራ እያስተዋወቁ-በዚያውም የክፍሉ/divisionን ስራን በአግባቡ ለመስራት ቀላል-ያደርገዋል።

ስለዚህ ሂደት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ እባካችሁ ይህን አቀራረብ/presentation ወይም የፌብሩዋሪ (Feb.) 9 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ፣ የስራ ክፍለ-ጊዜ የተካሄደበትን ይህን ቪዲዮ ተመልከቱ። በ6:30 p.m. ላይ በኤፕሪል (April) 20 ቀን 2023 ላይ በሚጀምረው-ስብሰባው ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ በዚህ ርዕስ ላይ ‘public hearing’ ያካሂዳል።

ቦርዱ የሚገኝበት የሂደት-ደረጃ፣ የባለድርሻ-አባላቶች (stakeholders) ድምፅ ወሳኝ-ሆኖ አስፈላጊ በሆነበት እና የማህበረሰብ አባላቶችን [የዳሰሳ-ጥናቱን ሞልተው-እንዲያጠናቅቁ እና ያላቸውን ሃሳብ እስከ ኤፕሪል (April) 26 ቀን 2023 ድረስ እንዲያካፍሉ]() የጋበዘ-ሲሆን፤ ይህንንም ቦርዱ ቀጣይ-እርምጃዎች ከመውሰዱ በፊት አካሂዷል። እነዚህ ለውጦች፤ በክንውኖች ቀጣይነት-ላይ፣ በነዋሪ ተወካይነት፣ ተጠያቂነት እና የምርጫ-ጊዜ ላይ፣ ተጽዕኖ ሊያመጡ-ይችሉ ይሆናል። በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ዙሪያ፣ የባለድርሻ-አባላት (Stakeholder) ሃሳብ - ለውሳኔዎች መግለጫ-ይሰጣል። አስተያየቶቻቸውን ለሰጡን-ሁሉ፣ እናመሰግናቸዋለን።

## በ‘Spring2ACTion’ ወቅት - በኤፕሪል (April) 26 ቀን 2023 ላይ፣ የACPS አጋር ድርጅቶችን መደገፍ




የ‘Spring2ACTion’ አሌክሳንድርያ - ዓመታዊ የመስጠት ቀን - እየተዳረሰ-ይገኛል! በኤፕሪል (April) 26 ቀን 2023 ላይ፣ በዚህ የ24-ሰዓት የኦንላይን ዝግጅት ላይ - ማህበረሰቡን የሚያበለጽጉ - በአሌክሳንድርያ ውስጥ ያለትርፍ-የሚሰሩ (nonprofits)ን የሚደግፍ እና የሚያከብር-ዝግጅት ላይ ሁሉም እንድካፈል-ተጋብዟል። የገንዘብ-እርዳታን ለማሰባሰብ - በ‘Spring2ACTion’ ዝግጅት-ውስጥ፣ በርካታ የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (ACPS) ፕሮግራሞች - ከአሌክሳንድርያ ፒቲኤ (PTA) ካውንስል እና የትምህርት ቤት ፒቲኤ (PTA) ክፍሎች ጋር ተጨማሪ-ሆነው የሚካፈሉ-ይሆናል። በቅድሚያ-የመስጠት ሂደቱ በ‘Spring2ACTion’ አማካኝነት - ከኤፕሪል (April) 12 ቀን 2023 ጀሮ የተጀመረ እና፣ ተሳታፊዎች አሁን በቀጥታ ወደ [Spring2ACTion ድህረ-ገጽ]() በመሄድ፣ ልገሳቸውን መስጠት-ይችላሉ።

የቤተሰብ እኩልነትን በACPS ውስጥ ወደ የላቀ-ደረጃ ለማድረስ በሚደረግ ቀጣይነት-ያለት ጥረቱ-አንዱ አካል ሆኖ፤ [የአሌክሳንድርያ ‘PTAC’፣ በዚህ ዓመት የ ‘Spring2ACTion ዘመቻ/campaign’ ውስጥ የሚካፈል-ሲሆን]() በጥቂት የመገኛ-ምንጮች ለሚከናወነው ለፒቲኤ (PTA) ክፍሎች የገንዘብ-እርዳታ የሚያሰባስብ-ይሆናል። የምታደርጉት ልገሣ - በአሌክሳንድርያ ውስጥ በይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ ልጆች አገልግሎት ለሚሰጠው - በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለቤተሰብ ተሣትፎ እንቅስቃሴዎች፣ የገንዘብ እርዳታን የሚያደግ-ይሆናል። [የትምህርት ቤት ክፍል/division የፒቲኤ (PTA) ክፍሎች/units፤ በግላቸው-ዝግጅቶችን ለማዘጋጀትም መመዝገበዋል (signed up)]() የተወሰኑ ግቦቻቸውን ለመርዳት-ሲሉ ተመዝግበዋል።

በ‘ACT for Alexandria’ የቀረበው - ‘Spring2ACTion’፤ በ13ኛው ዓመቱ ላይ የሚገኝ እና በይበልጥ-ግድ በሚላቸው እርታዎች ላይ - እርዳታ-ሰጪዎችን በማገናኛ ቀላል-መንገድን የሚፈጥር-ነው። ይህ የርቀት/virtual የገንዘብ-ማሰባሰቢያ ጥረት የተጀመረው በ2011 የሆነ-እና በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ከ70,000 ልገሣ-ሰጪዎች በላይ የሆኑ - በአጠቃላይ ድምሩ እስከ $17 ሚሊዮን የሚደርስ ልገሣዎችን በ‘Spring2ACTion’ በኩል አድርገዋል። የዚህ ዓመት ግብ፤ ከ$2.5 ሚሊዮን በላይ ለማሰባሰብ - እስከ 10,000 ልገሣ-ሰጪዎች እንዲሰጡ በማድረግ፣ እና 165 ተሳታፊ ድርጅቶችን በማሳተፍ ለማሰባሰብ-ነው።

የ‘ACT for Alexandria’ ዋና የፕሮግራም ሹም የሆኑት ብራንዲ ዪ (Brandi Yee) እንዳሉት፤ “ ‘Spring2ACTion’ - ስለ አዲስ ድርጅቶች የማወቂያ እና እገዛ-አድርጎ ለመርዳት የሚያስችል ዕድል ነው። እያንዳንዱ ልገሣ፣ መጠኑ ምንም-ሆነ ምን - አሌክሳንድርያ - በሁሉም-ነገር ዙሪያ - ጠንካራ፣ ሕያው ማህበረሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ-ነው። ከምንወደው ማህበረሰብ፣ መልሰን የምንሰጠን እናቅርብ።”

## የመጨረሻ-ዕድል: ለ'PTAC Golden Apple' ሽልማት - የACPS ትምህርት-ሰጪን - እስከ ኤፕሪል (April) 21 ቀን 2023 ድረስ - በእጩነት-ማቅረብ




የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (PTAC)፤ የ2023 የ'PTAC Golden Apple' ሽልማት እጩዎችን - ማስገባት እንዲጀመር እየጠየቀ-ነው። የ'PTAC Golden Apple' ሽልማቶች - ለየአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ትምህርት-ሰጪዎች፤ - ከወላጆች እና ከእንክብካቤ-ሰጪዎች ጋር አጋርነትን በመፍጠር፣ የእያንዳንዱን ተማሪ ያለሁን-አቅም እውን-ለማድረግ - በቤተሰብ ተሳትፎ የላቀ-ደረጃን ላስመዘገቡት - ትምህርት-ሰጪዎች የሚሸልም-ነው።

"በእውነተኛነት የመኖሪያ-ቤት/ትምህርት ቤት አጋርነቶችን በአንድ-ላይ አቀናጅቶ መስራት የቻሉ አስተማሪዎችን ብርሃን-ማንፀባረቅ በላይ የሚያስደስተን ነገር የለም፤" ብለዋል የአሌክሳንድርያ የ'PTAC' ፕሬዚዳንት - ሚሲ እስታብሩክ (Missy Estabrook)። "ይህ ወሳኝ-የሆነ ትብብር፣ ወደ ተማሪው ውጤታማነት፣ ባህሪይ፣ በትምህርት-ገበታ መገኘት እና በራስ-መተማመን ላይ መሻሻልን-ለማምጣት የሚመራ-ነው። ትምህርት-ሰጪዎቻችንን ለሚያደርጉት-ሁሉ ለማመስገን በመጓጓት - እስከምናመሰግናቸው መጠበቅ-ያቅተናል።"

አርብ፣ ኤፕሪል (April) 21 ቀን 2023 ላይ ሽልማት የሚሰጣቸውን፤ ምሳሌ-ሊሆኑ የሚችሉትን የPTAC Golden Apple እጩ አስተማሪን ለመምረጥ ጊዜ-ውሰዱ።

## 'Lab on Wheels' - የ'STEM-H' ዕድሎችን፣ ለACPS መካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች - አምጥቷል



የ'The Immersive Learning Center (ILC)' ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - መካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች - ሣይንስን፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ሂሳብ እና ጤና (STEM-H) የስራ-መስኮችን እንዲፈትሹ፤ በሩን-ከፍቷል። ወደ ጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ የሕክምና ትምህርት ቤት እና የጤና ሣይንስ እና የማህበረሰብ የ'Medi-Corps' ፕሮግራም ለማግኘት የሚያስችለው - ትልቅ ሰማያዊ ተሽከርካሪ፤ ለተማሪዎቻችን በብሄራዊ የጤና ተቋም (National Institutes of Health (NIH) የፓይለት ፕሮግራም የገንዘብ-እርዳታ ማካኝነት - እንዲሳካ አድርጎታል።

‘ILC’ - ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ግኝት የሆኑትን በርካታ-ነገሮች በ46-ጫማ ርዝመት ባለው ‘lab on wheels’ ላይ አድርጎ፣ ተማሪዎች ዘመናዊ-የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እንደ augmented and mixed reality to simultaneously interact with physical and virtual worlds - ያሉትን ለመጠቀም ቀርቧል። በቅርብ-ጊዜ የወጡ የመማሪያ ቴክኖሎጂዎችን ያካተተና - የትንታኔያዊ አስተሳሰብን ለመገንባት እና የተማሪን የመማር እና የመሣተፍ ሁኔታ ለመጨመር-አላማ- አድርጉ የሚሰራ ትምህርት የያዘ-ነው። ‘ILC’ ተመስርቶ-የነበረው፣ በ‘Growth and Opportunity Virginia grant’ ነው።

የ‘NIH’s Artificial Intelligence/Machine Learning Consortium’ የጤና እኩልነትን እና ምርምር ስብጥን የላቀ-ደረጃ የሚያደርስ (Advance Health Equity and Researcher Diversity (AIM-AHEAD) የገንዘብ-እርዳታው ትኩረት-የሚያደርገው፤ በአሁኑ-ጊዜ በሚገባ ያልተወከሉትን የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ/የማሽን መማሪያ ሞዴሎች (artificial intelligence/machine learning models)ን በማሳደግ ላይ ተሳታፊነትን እና የምርምር-ሰራተኞችን ውክልና ለማሳደግ ነው። የገንዘብ-እርዳታው አላማ-ያድረገው፤ በ‘STEM-H’ ላይ ያላቸውን ፍላጎት ለማጎልበት ተማሪዎችን ቀደም-ብሎ በማግኘት-ላይ ነው።



“በዘር ወይም በጎሳ አናሳ-ሆነው የተለዩ ታዳጊ-ወጣቶች - በርካታ-ስፋት ባላቸው የሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ሂሳብ እና የጤና ሣይንስ የስራ-መስኮችን ለማወቅ እና ለመዘጋጀት የሚችሉበት ሁኔታ-አነስተኛ-ነው፤” ብለዋል የ‘NIH AIM-AHEAD’ ፕሮግራም ማናጀር ኬሊ ብሩክዋይ (Kelly Brockway)። “እና፣ ተሰጥዖ/talent በየቦታው የሚገኝ-ቢሆንም፤ ዕድል ግን አይገኝም። ይህ ከትምህርት-ቤት በኋል ፕሮግራም፤ ለACPS ታዳጊ-ወጣቶች ባላቸው የማግኘት-ዕድል ላይ ያለውን ክፍተት-ለመዝጋት ሙከራ-የሚደረግበት ነው።”

ብሩክዋይ (Brockway) ሲገልጹ፤ በመካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎችን ወደ ‘STEM-H’ እንዲያውቁት-ማቅረብ፤ ያልተፈተሸ ፍላጎት እንዳላቸው እንዲያውቁ-ሊያደርጋቸው ይችላል። “ተማሪዎች ይህን ቴክኖሎጂ ይወዳሉ፣ ዛሬ የሚማሩበት መንገዳቸው ነው፣” ብለዋል - ብሩክዋይ (Brockway)። “እየሰሩ-የሚማሩበት ሁኔታ-ነው ያላቸው፣ እና ይህም፣ እንዳለ-ያላወቁትን መንገዶችን እንዲፈትሹ ዕድል-ይሰጣቸዋል። ይህ በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) ውስጥ፣ በሚመርጡዋቸው ኮርሶች ላይ መሪ-ሆነው እንዲመራቸው ይረዳቸዋል።”

ብሩክዋይ (Brockway) ጨምረው-ሲናረጉ፤ የ‘ILC’ ከፍተኛ-ደረጃ ያለው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ - ተማሪዎች ሰፊ የሆነ የጤና የስራ-መስኮችን በክፍል-ውስጥ በሌሉ እንቅስቃሴዎች እና አፕሊኬሽኖች/applications አማካኝነት እንዲፈትሹ ያስችላቸዋል። “ተማሪዎች በማሽጋገሪያ የትምህርት ተሞክሮዎች አማካኝነት ኃይል-የሚያገኙ ናቸው። የ‘ILC champions life and health sciences and technology’፣ ምኞቶችን ከፍ-የሚያደርግ፣ የትንታኔ አስተሳሰብ ችሎታን እና የትብብር ስራን ለማዳበር ይረዳል።

የጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት (GWMS) - ከትምህርት-ቤት በኋላ ክለብ አባላቶች፤ ከ‘ILC’ ምትክ - ቴክኖሎጂን የመፈተሽ ዕድል ነበራቸው። “ይህ ተማሪዎችን በተለያዩ መስኮች የመፈተሻ መንገድ ነው፤” ብለዋል ማቲው ሜሊስ (Matthew Mellis) - የ‘GWMS’ የስምንተኛ ክፍል የሣይንስ አስተማሪ እና የክለቡ አድቫይዘር። “ሁሉም-ነገር፤ በዕይታ/visuals እና በመመልከትና በመስራት ላይ የተመረኮዘ-ነው።”

በፕሮግራሙ ውስጥ የሚካፈሉ ተማሪዎች፤ እንደ ዞዪ ጋርሲያ ጂሜንዝ (Zoe Garcia Jimenez) ያሉት ሲናገሩ - በቴክኖሎጂ የሚማርክ ነገርን እዳገኙ እና ሲያብራሩት፤ “የጨመረው እውነታ/augmented reality፣ የሆሎግራምስ ጥቅም/the use of holograms፣

ለመፈተሽ-ግሩም የሆነ መንገድ ነው/is a great way to explore።” ናታሊአ ሆልቤክ (Natalia Holbeck)፣ 3-Dን ተጠቅሞ የሰውን አፅም ማጥናት - ሁሉንም የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ለመማር የረዳት-ሆኖ አግኝተዋለች። ሪስ ዋተርሃውስ (Reese Waterhouse) - በባዮ-ቴክኖሎጂ (bio-technology) ያላትን ፍላጎት፣ ፕሮግራሙ እንደቀሰቀው ተናግራለች። በ‘STEM-H’ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሴት-ልጆች የምታበረታታ-ናት፤ “አዲስ-ነገሮችን ምን-ሊሰጡ እንደሚችሉ ለመፈተሽ እንዳይፈሩ።”

የከትምህርት-ቤት በኋላ ክለቡም - በጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ፣ እና ተጨማሪ ክለቦች በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት እና በፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከK-8 ትምህርት ቤት ውስጥ የሚዘጋጁ-ይሆናሉ። በቀለም-ትምህርቱ ዓመት ማብቂያ-ላይ፤ ግብ-የሆነው ‘ILC’ በሁሉም አራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጉብኝት እንዲያደርግ እና ስለ ‘STEM-H’ እንቅስቃሴዎች መሳጭ-በሆኑ ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት - ተማሪዎች እንዲፈትሹ-ለማድረግ ነው።

የ‘NIH AIM-AHEAD’ የገንዘብ-እርዳታ - ፕሮግራሙን በገንዘብ-የሚያግዘው፤ የአንድ-ዓመት ፓይለት/pilot አንዱ-አካል ሆኖ በሴፕቴምበር (September) 2023 ይጠናቀቃል። ACPS እና የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ የሕክምና እና የጤና ሳይንስ ትምህርት ቤት (The George Washington University School of Medicine and Health Sciences)፤ የገንዘብ-እርዳታውን ለአስር-ዓመታት በ$2 ሚሊዮን በዓመት እንዲቀጥል የቀረበውን-ሃሳብ ለማስገባት ያቅዳል። የገንዘቡ መጠን፣ ለመካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች የበለጠ-አስተዋጽዖ የሚያገኙበትን ሁኔታን ፕሮግራሙ እንዲያቀርብ ያደርገዋል።

“ይህ ለዚህ-ብቻ የቀረበው የገንዘብ-እርዳታ - ከክፍል/division ትኩረት ያደርገ የSTEM discovery እና የስራ-መስክ ፍለጋ በጥሩ-ሁኔታ ጎን-ለጎን ሆኖ ስለሚሄድ - በጣም ልዩ-የሆነ ነው፤” ብለዋል፣ የACPS የገንዘብ-እርዳታዎች እና የአጋርነቶች - ስራ-አስኪያጅ፣ ግሬግ ታርዴው (Greg Tardieu)። “የ‘AIM-AHEAD Southeast Hub’ መሪ አኒል ሻንከር (Anil Shanker) PhDን መካሪነት/mentorship እና አመራርን-በመስጠታቸው -እና የቡድን-አባላቶችን፣ ኪንጉ ዋንግ (Qingguo Wang)፣ PhD፣ ራቢር ሲንግ (Rajbir Singh)፣ MBBS እና ስምሩቲ ሞሃንቲ (Smruti Mohanty) MSc, MBA፤ በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ እንቅስቃሴዎችን በማስተባበራቸው እውቅና-መስጠት እንወዳለን፤” ብለዋል ታርዴው (Tardieu)።

## ACPS - የበጋ ትምህርት ምዝገባን - ለሁሉም ጀምሯል




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ የበጋ ማበልጸጊያ ፕሮግራሞቻችንን ለሁሉም በአሁኑ-ጊዜ ለሚገኙ ከPreK-8 ተማሪዎች ማቅረቡን-መቀጠሉን ሲያስታውቅ ደስታ-ይሰማዋል። አሁንም-ሌላ በእጅ-እየሰሩ የሚማሩበትን የበጋ (summer) ማበልጸጊያ ተሞክሮችን በማቅረባችን ደስታ-ተሰምቶናል፤ እና ሁሉንም የACPS ከPreK-8 ተማሪዎችን ወደ ነፃ የበጋ (summer) ትምህርት ፕሮግራሞች እንዲመዘገቡ እንጋብዛለን።

ወደ እነዚህ ፕሮግራሞች መመዝገቢያ ጊዜ - ለሁሉም ተማሪዎች ከ8 a.m. አርብ ኤፕሪል (April) 14 ቀን 2023 ይጀምር-እና፣ በ11:59 p.m. እሁድ፣ ሜይ (May) 14 ቀን 2023 ላይ ያበቃል። ቤተሰቦች ቀደም-ብለው እንዲመዘገቡ አበክረን-እናበረታታለን፣

ይህም-የሆነበት በበጋ ትምህርት (summer learning) ውስጥ ልናገለግላቸው የምንችለው ተማሪዎች ቁጥር፣ በአሉን የበጋ (summer) ትምህርት ቤት ቦታ እና የሠራተኞች-ብዛት አቅም ላይ ተመስርቶ የሚወሰን በመሆኑ ነው። ልጆቻቸውን ወደ በጋ ትምህርት (summer learning) ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ቤተሰቦች፤ የACPS የበጋ ትምህርት (Summer Learning) 2023 ድህረ-ገጽን መጎብኘት አለባቸው።

የበጋ ትምህርት (summer learning) ተሞክሮው ትኩረት-የሚያደርገው፤ በሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ (Science, Technology, Engineering, and Math (STEM) - ከK-4 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች እና የስራ-መስክ ፍሊጋን ከ5-7 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች በማቅረብ ላይ ነው። በስምንተኛ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ በአካል-ተገኝቶ በሚሰጠው የሙዚቃ እና የቲያትር ካምፖች ውስጥ፤ እንዲሁም በኦንላይን-በሚሰጠው በካንቫስ/Canvas ኮርስ በሆነው በጤና & PE 9 መመዝገብ-ይችላሉ። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በአካል-ተገኝቶ (in-person) የበጋ ትምህርት (summer learning) ፕሮግራም፤ የክሬዲት መልሶ-ማነሳሻ (credit recovery) ኮርሶች ለሚያስፈልጓቸው ተማሪዎች-ብቻ፣ ክፍትይሆናል። አዲስ የክሬዲት ኮርሶች፤ በኦንላይን አቅራቢ (online vendor) አማካኝነት ትምህርት-የሚሰጥ ይሆናል።

የACPS የበጋ ትምህርት (Summer Learning) 2023 - የአራት-ሣምንታት በአካል-ተገኝቶ መማርን፣ ከጁን (June) 26 ቀን - ጁላይ (July) 20 ቀን 2023 የጊዜ-አቀማመጥን ያካተተ ይሆናል። ትምህርቱ፤ ዘወትር ሰኞ ቀናት ጀምሮ እስከ ሐሙስ-ቀናቶች በየሣምንቱ የሚሰጥ ሲሆን፣ አርብ-ቀናቶች ላይ ትምህርት የለም። ሐሙስ፣ ጁላይ (July) 4 ቀን 2023 ላይም፣ ትምህርት የለም።

የበጋ (Summer) ትምህርት ሰዓታት - እንደሚከተሉት ናቸው:

- **PreK እና ከK-4 ክፍሎች** (Young Scholars'ን ጨምሮ): ከ8 a.m.-12 p.m.
- **የሁለት-ቋንቋ (Dual-Language):** ከ8 a.m.-12 p.m.
- **ከ5-7 ክፍሎች፣ የሁለት ቋንቋ የበጋ መሸጋገሪያ (Dual Language Summer Bridge)፣ የቲያትር ካምፕ/Theatre Camp:** ከ8:45 a.m.-1 p.m.
- **ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የሙዚቃ ካምፕ (Music Camp)**: ከ9:30 a.m.-2:30 p.m. (በአካል-ተገኝቶ የሚሰጡ-ክፍሎች፣ ብቻ)
- **ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - ኦንላይን**: ቀናቶች እና ሰዓታት የሚለያዩ እና መለዋወጥ-የሚችሉ
- **ልዩ ትምህርት (Special Education):**
  - የPreK ክፍሎች: ከ9-11 a.m.
  - ከK-12 እና ከምርቃት በኋላ ክፍሎች/post graduate classes: ከ9 a.m.-1 p.m.

የሚከተሉት ፕሮግራሞች የተለያየ ቀናቶች ሊኖራቸው እንደሚችል እባካችሁ አስታውሱ: ሙዚቃ እና ቲያትር ካምፖች፣ የባለ-ሁለት ቋንቋ የበጋ መሸጋገሪያ (Dual Language Summer Bridge)፣ የከፍተኛ ደረጃ የኦንላይን እና የ'Child Find' የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች። እባካችሁ፤ የACPS የበጋ ትምህርት (Summer Learning) 2023 ድህረ-ገጽን፣ ልዩ-መረጃዎችን ለማግኘት፣ ጎብኙ። መጓጓዣ/transportation ለማግኘት እንዲችሉ፤ እስከ ሜይ (May) 14 ቀን 2023 የማብቂያ-ቀን እስከሆነው ድረስ፣ ተማሪዎች መመዝገብ-አለባቸው።

በአሁኑ-ጊዜ የPreK ተማሪዎች፤ በ'exploring the five senses' ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። በአሁኑ-ጊዜ፣ ከK-4 ክፍሎች ውስጥ ያሉት የመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ የ'Camp Inventions ስርዓተ-ትምህርት'ን ተጠቅመው፣ በ'STEM' መማር ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ተማሪዎች በራስ-መተማመን እና ጽናትን የሚያገኙ፣ የSTEM ችሎታቸውን የሚገነቡ፣ እና በ'collaborative and creative problem-solving' እንቅስቃሴ አማካኝነት - እንደ Catching Air, Mimic Bot እና "Fair Games" የሂሳብ ካርኒቫል (math carnival) ባሉት ውስጥ፣ የንባብ ችሎታቸውን ያሻሽላሉ። ወጣት-ታዳጊ (Young Scholars) ተማሪዎች፣ በመጀመሪያ-ደረጃ የበጋ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የሚቀላቀሉ እና በ'Camp Invention' ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ይካፈላሉ።

የ'Career Exploration Camp' የዚህ-ዓመት ገጽታ/theme፤ በአሁኑ-ጊዜ ከ5-7 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን - በእጅ-እየሰሩ የሚሞክሩትን፣ በፕሮጀክት-ላይ መሠረት ያደረገ የEngineering is Everywhere ስርዓተ-ትምህርትን ይጠቀማሉ።

የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች፣ በHere Comes the Sun፣ Outbreak Alert፣ Shake Things Up እና The Sky's the Limit ውስጥ ይካፈላሉ። የስድስተኛ እና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች፤ በLight Up the Night፣ Plants to Plastics እና በIt's About Time ውስጥ ይካፈላሉ።

ሁለቱም የመጀመሪያ-ደረጃ እና የመካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች፤ የእንግሊዘኛ ቋንቋ በተለያየ-ክፍል መከፋፈል/scaffolds እና የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ (English Learner) በየዕለቱ የትምህርት-አሰጣጥ ውስጥ ያላቸውን ተመራጭ-የሆነ ተሞክሮዎችን የሚያቀርብ-ይሆናል። የልዩ ትምህርት (Special education) እርዳታ-ሰጪ አስተማሪዎች፣ የክፍል-ውስጥ አስተማሪዎችን ከK-12 ክፍሎች ውስጥ - የቀረበውን ስርዓተ-ትምህርት በመጠቀም ተመራጭ-የሆነ ተሞክሮዎችን በመለየት እና ተማሪዎችን እንደየአስፈላጊነቱ በመርዳት እገዛ-ያደርጉላቸዋል። የተራዘ የትምህርት ዓመት/Extended School Year (ESY) የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪዎች፤ የ'ESY' አገልግሎት ደቂቃዎችን - በ'ESY' የየግል የትምህርት ዕቅዱ ላይ በተዘረዘረው-መሠረት ይሰጣሉ። የልዩ ትምህርት (Special education) ጣልቃ-ገብነት አስተማሪዎች፤ የተወሰኑ የማንበብ እና የሂሳብ ጣልቃ-ገብነቶች ፕሮግራሞችን በመጠቀም ለተማሪዎች ትምህርት-ይሰጣሉ። ሁሉም የበጋ (summer) ትምህርት ፕሮግራሞች፤ በቦታው የሚገኙ ካውንስለሮች፣ ማህበራዊ-ሠራተኞች (social workers) እና ነርሶች - ለተማሪዎች በሚያስፈልጓቸው የማህበራዊ-ስሜታዊ እና/ወይም በሕክምና እርዳታዎች ለመርዳት የሚገኙ-ይሆናል።

የባለ-ሁለት ቋንቋ (dual language) የበጋ ቋንቋ አካዳሚ (summer language academy)፣ ትኩረት የሚያደርገው፤ በሁለቱም በፕሮግራም ቋንቋዎች - የስፓኒሽ ቋንቋ ተናጋሪ አገሮችን ታሪክ፣ የጂኦግራፊ-አቀማመጥ፣ እና አካባቢን በማጥናት- በአሁኑ-ጊዜ ከK-4 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ የሁለት-ቋንቋ (dual language) ተማሪዎች፣ የማበርጸጊያ ተሞክሮዎችን እንዲያገኙ-ያደርጋል። የባለ-ሁለት ቋንቋ የበጋ መሸጋገሪያ (Dual Language Summer Bridge) ፕሮግራም፤ በአሁኑ-ጊዜ በአምስተኛ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ወደ መካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ለሚሸጋገሩ እገዛ-ለመስጠት - ዕለታዊ ትምህርቶችን የሚያቀርብ-ነው። ይህ ፕሮግራም ከጁላይ (July) 10-20 ቀን 2023 ድረስ፣ በጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ ይካሄዳል።

የሙዚቃ ካምፕ፤ በአሁኑ-ጊዜ ከ4-8 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች - ደረጃ በትክክለኛ-መንገድ በጠበቀ የሙዚቃ መሣሪያ - ከጁላይ (July) 10-20 ቀን 2023 ድረስ፣ በአሌክሳንድርያ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School - ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) ያስተምራል። ካምፑ፤ የመጨረሻ ዝግጅቱን - ሐሙስ ጁላይ (July) 20 ቀን 2023 ላይ የሚያቀርብ-ይሆናል። የቲያትር ካምፕ፤ በአሁኑ-ጊዜ ከ6-8 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች - በጆርጅ ዋሽንግተን መካከለኛ-ደረጃ ትምርህት ቤት ውስጥ ከጁን (June) 26-ጁላይ (July) 13 ቀን 2023 ድረስ ይካሄዳል (ሐሙስ፣ ጁላይ/July 4 ቀን 2023 ላይ ካምፕ-አይኖርም)። ተማሪዎች ስለ መድረክ ላይ-ትወና፣ እንዲሁም በርካታ የቲያትር አካል የሆኑ ቴክኒኮችን - እንደ ዲዛይን እና መገንባት፣ መብራት፣ ድምጽ፣ የትወና-አልባሳቶች እና ሜክ-አፕ (make-upን ለመማር ዕድል ይኖራቸዋል።

ተጨማሪ መረጃዎችን እና አዲስና ማሻሻያዎችን (updates) ለማግኘት፣ የACPS Summer Learning 2023 ድህረ-ገጽን፣ ጎብኙ።

# አሌክሳንድርያ፤ በአራት የACPS ትምህርት ቤቶች አቅራቢያ - የፍጥነት-መቆጣጠሪያ ካሜራዎችን ሊተክል-ነው




የመኪና-ፍጥነት ካሜራዎች (Speed cameras)፤ በዚህ ፀደይ (spring) ወቅት ላይ፣ በአራት የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) አቅራቢያ-ይተከላሉ:

- የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት - በ'Seminary Road' ላይ - በ'Kenmore Avenue' እና በ'North Jordan Street' መካከል።
- ጆን አዳምስ (John Adams) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት - በ'North Beauregard Street' ላይ - በ'North Highview Lane' እና 'Reading Avenue' መካከል።
- ጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት - በ'Mount Vernon Avenue' ላይ፣ በ'Braddock Road' እና በ'Luray Avenue' መካከል።

ACPS፣ የአሌክሳንድርያ ፖሊስ መምሪያ (Alexandria Police Department) እና የአሌክሳንድርያ የትራንስፖርት እና አካባቢ አገልግሎቶች መምሪያ (Alexandria Department of Transportation and Environmental Services) በትብብር-በመስራት፣ የፍጥነት-መቆጣጠሪያ ካሜራው (speed camera) የሚሆኑበትን ቦታ በመምረጥ ሠርተዋል። በዚህ ፀደይ-ወቅት (spring)፣ የፍጥነት-መቆጣጠሪያ ካሜራዎቹ (speed cameras) ከተተከሉ-በኋላ፤ የሙከራ-ሂደታቸው የሚካሄድ-ሲሆን እና በዚህ ወቅት ለአስከርካሪዎች በሚተላለፉ-ጊዜ የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል። ፕሮግራሙ ሙሉ-ለሙሉ የሚጀምረው፤ በ2023-24 የትምህርት ዓመት ላይ ሲሆን፣ በዚያን ጊዜ የሚሰጡ የጥሰት-ቅጣቶች ነጥብ-ያስቆጥራሉ።

የአሌክሳንድርያ የከተማው ምክር-ቤት (The Alexandria City Council)፣ ይህ የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎች በትምህርት ቤት ዞኖች ውስጥ ለማስገባት፤ እንደ ዓመታዊ የ2023 የከተማ በጀት አንዱ-አካል አድሮ በገንዘብ-እርዳታው ውስጥ አካትቶታል። ውሳኔው የተደረገው፤ ከተማዋን Vision Zero ግቡን ጠብቆ-ለማቆየት እና አደገኛ እና ለህልፈት-የሚያደርጉ አደጋዎችን እስከ 2028 ድረስ ባለው-ጊዜ ለማጥፋት-ነው። እንደ የአሜሪካ የትራንስፖርት መምሪያ (U.S. Department of Transportation) መረጃ መሠረት፣ የፍጥነት-መቆጣጠሪያ ካሜራዎች (speed cameras) ፍቱን-የሆነ የደህንነት-መጠበቂያ መከላከያ-እርምጃ የሆኑ እና፣ የግጭት-አደጋዎችን ከ50% በላይ መቀነስ-ይችላሉ።

አሌክሳንድርያ፤ ከበርካታ በቨርጅኒያ ዙሪያ ያሉ፤ የፍጥነት-መቆጣጠሪያ ካሜራ (speed camera) ፕሮግራምን ከሚያስፈጽሙ-ጋር በጋራ-ይሰራል። በ2020፣ የ'Commonwealth of Virginia' በትምህርት ቤት እና በስራ ዞኖች አካባቢ፣ የፍጥነት-መቆጣጠሪያ ካሜራዎች (speed cameras)ን ለመጠቀም ፈቃድ-መስጫ ሕግን-አሳልፏል።

# ኤፕሪል (April) 29 ቀን 2023: “የእናንተ-ወደፊት በዛሬው-ዕለት/Your Future Today” - የ‘Mentoring Saturday’ ዝግጅት



ቅዳሜ፣ ኤፕሪል (April) 29 ቀን 2023 ላይ፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ የመጀመሪያ-የሆነውን የ‘mentoring Saturday’ ዝግጅቱን - በ“የእናንተ-ወደፊት በዛሬው-ዕለት/Your Future Today” በሚል፤ ወደ ጥቁር/አፍሪካዊ አሜሪካውያን - ከ8-12ኛ ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ወንዶች ያተኮረ-ሆኖ የተዘጋጀውን-ዝግጅት ያዘጋጃል። ይህ ዝግጅት፤ ከ“ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም/Equity for All’ ጋር ትኩረት የሚያደርገውን የACPS ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan)ን በማያዝ፤ ልዩ-በሆኑ የጥቁር ወንዶች ታዳጊዎች ላይ የሚያስፈልጋቸውን-ነገሮች ለማስገኘት፤ እውቅናን እና የመካሪነት-አገልግሎቶችን የሚፈጥር-ዝግጅት ነው። የመረጃ-ስብስባችን እንደሚያሳየው፤ በእዚህ ቡድን ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ በዲስፕሊን ውጤቶች፣ በእስራቶች/መያዞች እና በቀለም-ትምህርት ልዩነቶች ላይ - ተመጣጣኝ-ባልሆነ ሁኔታ የተካተቱ መሆኑን ያሳያል። ጠንካራ-የሆነ የመካሪነት ግንኙነቶችን በማሳደርግ፣ አንዳንድ ጥቁር ታዳጊ ወንዶች እየተጋፈጧቸው ያሉትን አስቸጋሪና-ፈታኝ ነገሮችን ለመቀነስ የሚያስችል፣ እና የማህበረሰቦች፣ ቤተሰቦች እና የባህሎች ጠንካራ-ጎኖች ከፍ-ከፍ ተደርገው ያላቸውን የስኬታማነት ማግኘት-ሁኔታ ወደ-ላይ ከፍ አድርጎ ለማበረታታት የሚረዳ-ይሆናል።

የ“Your Future Today” ዝግጅት - በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ - (4646 Seminary Road) ከ9 a.m. እስከ 1 p.m. ድረስ የሚካሄድ-ዝግጅት ነው። አንዳንድ-የቀኑ እንቅስቃሴዎች ሆነው የሚካተተቱ:

- ቁርስ እና፣ ከእኩዮች ጋር ኔትወርክ/network ማድረጊያ-ጊዜ።
- ከጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ እና ከትምህርት ቤት ቦርድ አባላቶች የእንኳን-ደህና መጣችሁ አቀባበል።
- ከጥቁር ወንድ ምክር-ሰጪዎች (Black male mentors)፤ ጥበብ-የተሞላበት ውሳኔዎችን መወሰን፣ ሕግን መረዳት እና እንቅፋቶችን በመወጣት ላይ - የሚናገሩትን የማዳመጥ ዕድሎች።
- የገንዘብ-አያያዝ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ።
- የስነ-ምግባር/Etiquette ክፍለ-ጊዜ (ምሣን ጨምሮ)።

ይህ ዝግጅት የተቀረጸው፤ ለጥቁር/አፍሪካን አሜሪካውያን ወንዶችን - ልዩ ሆኖ የሚያስፈልጓቸውን -ነገሮች ለማሟላት የተቀረጸ ዝግጅት ሲሆን፤ ሆኖም-ግን፣ ሁሉም ከ8-12ኛ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ለመመዝገብ ይችላሉ። ወደዚህ ዝግጅት ተማሪዎችን ለማስመዝገብ ፍላጎት ካላችሁ፤ እባካችሁ የምዝገባ ቅጹን በኦንላይን ላይ፣ ሞልታችሁ-አጠናቅቁ።

# የኤፕሪል (April) 20 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



በ6:30 p.m.፣ በኤፕሪል (April) 20 ቀን 2023 ላይ በሚጀመረው ስብሰባው ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርድ - ወደ 'ተለዋዋጭነት-ያለው ተርሞች/staggered terms'፣ (በዚህ የACPS ዕትም ላይ ተዛማጅ-የሆኑ ጽሁፎችን ተመልከቱ) የትምህርት ቤት ቦርዱ ባለው መዋቅር ላይ ለውጥ-የማድረግን ሁኔታ በ'public hearing' ላይ የሚያካሂድ-ይሆናል፣ እና የሚከተሉትን ርዕሶች ላይ በቦርድ-ስብሰባ አጀንዳ-አድርጎ ይዟል:

- ከትምህርት ቤት ጤና አማካሪ ቦርድ፣ የአድቫይዘሪ ኮሚቴ አስተያየቶች
- የአትሌቲክ ፕሮግራም አዲስና-ማሻሻያ (update)።
- በ'CIP reserve' ላይ እና የሦስተኛው ኢጋማሽ/third quarter ሪፖርቶች።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

# በኤፕሪል (April) 6 ቀን 2023 ላይ፣ የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ኤፕሪል (April) 6 ቀን 2023 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 25.09 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በኤፕሪል (April) 6 ቀን 2023 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ-ይመለከታል።